ክፍል 2 የግለሰብ ነፃነትን ማክበር

ሀ. የንግግርና የኘሬስ ነፃነት

ምንም እንኳን ሕገ-መንግሥቱም ሆነ ያገሪቱ ህግ የንግግር የኘሬስ ነፃነትን ያጐናፀፉ ቢሆንም መንግሥት በተግባር እነዚህን መብቶች ገድቧቸዋል። መንግሥት ጋዜጠኞችን፣አሣታሚዎችንና አዘጋጆችን የፈጠራ ያላቸውን መረጃዎች በማሳተማቸውና የፕሬስ ህጉን በመጣስ ወንጀል ሲከስና ሲያዋክብ ቆይቷል። መንግሥት ሁሉንም በሞገድ የሚተላለፉ ሚዲያዎች መቆጣጠሩን ቀጥሎ ነበር። የግልና የመንግሥት ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ ራሳቸውን ሳንሱር ማድረግ ነበረባቸው።

በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙሀን ባብዛኛው የመንግሥትንና የገዢውን ፓርቲ የኢሕአዴግን አቋም የሚያንፀባርቁ ነበሩ። ይሁን እንጂ በቀጥታ የሚተላለፉ የሬዲዩና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች አንዳንዴ ቀጥታ የፓርላማ ክርክሮችንና የተቃዋሚ የፓርላማ አባላት አቋሞችን ልክ እንደ መንግስት ጋዜጦች ሁሉ ያቀርቡ ነበር። በመንግሥትና በግሉ ፕሬስ መሃከል የነበረው ግንኙነት ከምርጫው በኋላና በሰኔና ሕዳር 2005 ብጥብጦች ወቅት የበረውን ያህል የሻከረ ባይሆንም አብዛኛው በ2005 ይንቀሳቀሱ የነበሩት የግል ሚዲያዎች የጋዜጠኞችን እስርና መከሰስ ተከትሎ በመዘጋታቸው ወይም በራሳቸው ላይ ሳንሱር በማድረጋቸው ፀጥ እንዲሉ ተደርገዋል።

በሜይ 2005 የተጀመሩት የመንግሥት እርምጃዎች ብዙዎቹን የግል ጋዜጦች ፀጥ አሰኝተዋል። ያገር ውስጥ ጋዜጠኞች በመንግሥት ተደጋጋሚ መዋከብ እንደሚደረስባቸው እንዲሁም አታሚዎች ጋዜጦቻቸውን እንዳያትሙ ጫና ይደረግባቸው እንደነበር ያማርራሉ። በዚህም ምክንያት ከምርጫው በፊት እስከ አመቱ መጨረሻ የነበሩት የግል ጋዜጦች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ አሽቆልቁሏል። አሳታሚዎቻቸውና ዋና አዘጋጆቻቸው ከታሠሩ በኋላ ስምንት ጋዜጦች ታግደዋል። ስድስት ሌሎች ጋዜጦች ደግሞ በዚሁ የመንግሥት ርምጃ ምክንያት ወይም የመንግሥት ማተሚያ ቤቶች ጋዜጦቻቸውን አናትም ስላሉአቸው ሕትመት አቁመዋል። የተዘጉት ጋዜጦች ባንነድነት በሳምንት ወደ 400,000 ኮፒዎችን ያሠራጩ ነበር። ይህን የመንግሥት ርምጃ ተከትሎ ከቀሩት ስድስት የአማርኛ የፖለቲካ ጋዜጦች ባንድነት ወደ 40,000 ቅጂዎች ብቻ በስርጭት ላይ ነበሩ።

አልፎ አልፎ የውጪ ጋዜጠኞች መንግሥትን የሚተቹ ፅሁፎችን የሚፅፉ ቢሆንም ዘገባቸውን እራሳቸው ሳንሱር እንዲያደርጉ በመንግሥት ጫና ይደርስባቸው ነበር። ባመቱ ውስጥ ጥቂት ዘጋቢዎች መንግሥትን የሚተቹ ፅሁፎች በማሳተማቸው ካገር ተባረዋል።

ጃንዋሪ 21 ቀን የአሶሲየትድ ፕሬሱ ዘጋቢ አንቶኒ ሚቼል በአዲስ አበባ ውስጥ በተቃዋሚዎችና በፖሊስ መሃከል ደግሞ ስላገረሸው ግጭት በዘገበ ማግስት በ24 ሰዓታት ውስጥ ሃገሪቱን ለቆ እንዲወጣ ተደርጓል። የመንግሥት ንብረት የሆነው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ) መንግስት ሚቼል እንዲባረር የወሰነው "የጋዜጠኝነት ስነ ምግባርን በመፃረር በተደጋጋሚ ጊዜ ያገሪቱን ምስል በማንቋሸሹ" እንዲሁም "ስለኢትዮጵያ ከእውነት የራቀ መረጃ በማሠራጨቱ" ነው ብሏል። የውጪ ዜጋ የነበረውና ለተባበሩት መንግሥታት ዜና አገልግሎት ለኢሪን የሰራው ሚቼል ባገሪቱ ከአምስት አመታት በላይ ሰርቶ ነበር።

የፌብሯሪ 21 ቀን ደግሞ የውጪው ጋዜጠኛ የኢኒጐ ጊልሞር የጋዜጠኝነት ፈቃድ በማስታወቂያ ሚኒሲቴር ታግዷል። በታህሳስ 2005 "የኢትዮጵያው መሪ በሰብዓዊ መብት ምክንያት ተከሰሱ" በሚል ርዕስ ዘ አብዘርቨር

በተባለው የብሪታኒያ ጋዜጣ ላይ የዘገበው ዘገባ ከምርጫው በኋላ ተከሰቱ የተባሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ያካተተ ነበር።

ጁን 23 የሳምንታዊውን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ጋዜጣ የ"ዘላብ ሰሀራን ኢንፎርመር ሕትመት የቢሮ ለውጥ ማድረጉን አላሳወቀኝም በሚል የማስታወቂያ ሚኒስቴር አግዷል። ይሁን እንጂ ጋዜጣው ሁሉቱም በፅሁፍ የቢሮ ለውጥ ማድረጉን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አሳውቆ ነበር። በኦገስት 18 ሕትመቱን እንደገና እንዲቀጥል ፍቃድ አግኝቷል።

በየካቲት 10 የመጀመሪያውን የሥርጭት ፈቃድ በመስጠት ሁለት የግል ሬዲዮ ጣቢያዎች ባገሪቱ ስራ እንዲጀምሩ ፈቅዷል። ባመቱ መጨረሻ ሁሉቱም ሬዲዮ ጣቢያዎች ስራ አልጀመሩም ነበር። የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኤጀንሲ ሁሉቱን ጣቢያዎች፣ ዛሚ ፕብሊክ ኮኔክሽንንና ትንሳኤ ፋይን አርትስን፣ ከ12 ተፎካካሪዎች መሀል ባቀረቡት የገንዘብ አቅምና በፕሮግራሞቻቸው ይዘት እንደመረጣቸው አስታውቋል።

በኦገስት ወር የደቡብ ክልላዊ መንግስት ስድስት የኤፍ ኤም ጣቢያዎችን በማቋቋም ስርጭት ለመጀመር ዕቅድ እንዳለው አስታወቀ። በዚያው ወር የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኤጀንሲ በደቡብ ክልላዊ መንግስት ወስጥ ለሚገኘው "ኮሪ" ለተሰኘው የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ ፈቃድ ሰጥቷል።

ኦገስት 25 ቀን የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኤጀንሲ ከኢሕአዴግ ፓርቲ ጋር ግንኙነት ላለው ለራዲዮ ፋና የንግድ ፈቃደ ሰጠ። የኢትዮጵያ ሬዲዮም ለግል ቡድኖችና ግለሰቦች ለማስታወቂያና ሌሎች ፕሮግራሞች የአየር ጊዜ ሽጧል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ የአምስት ሰዓት የኤፍ ኤም ሬድዮ ስርጭትና የ3 ሰዓት ያገር ውስጥ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ስርጭት በቀን ሁለቱ ከዋና ከተማው ማድረጉን ቀጥሎ ነበር።

ብቸኛውን የቴሌቪዥን ጣቢያ ሥራ መንግሥት ያካሂድ የነበረ ሲሆን የዜና ስርጭቶችንም በጥብቅ ይቆጣጠር ነበር። የብሮድካስት ህጉ ግን ማንኛውም የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖት ድርጅት የማሰራጫ ጣቢያ ባለቤት እንዳይሆን ያግዳል። ህጉ በተጨማሪም የውጭ ዜጐችን ከባለቤትነት ያግዳል።

ባመቱ የአለም አቀፍ ዜና ማሠራጫዎች ገደብ ነበረባቸው። የቪኦኤ ስርጭት ሆን ተብሎ እንዳይተላለፍ ይደረግ ነበር። መንግሥት ግለሰቦች የሳተላይት መቀበያ ዲሾች እንዲኖራቸው ፈቅዶ ነበር። ነገር ግን የዋጋው ውድነትና የኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽንስ ኮርፖሬሽን ውሱን አቅም ይህንን ቴክኖሎጂ ባግባቡ መጠቀም እንዳይቻል አድርጓል።

መንግሥት የጋዜጠኞችን እስር አግባብነት ለማሳየት ሃሰተኛ መረጃን በማሳተም፣ የብሔር ጥላቻን በመቀስቀስና በስም ማጥፋት ወንጀሎች ላይ ያሉ የህጉን አንቀጾች መጥቀሱን ቀጥሏል። ከተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ጋር 16 ጋዜጠኞች ባገር ክህደት፣ በዘር ማጥፋትና ሕገ-መንግሥቱን ለመናድ በመሞከር ወንጀል የተከሰሱ ሲሆን ወንጀለኛ ሆነው ከተገኙ እነዚህ ክሶች ከፍተኛውን የዕድሜ ልክ እስራት ወይም የሞት ፍርድ የሚያስፈርዱባቸው ናቸው።

በኖቬምበር 2005 አምስት የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጋዜጠኞች ከቅንጅቱ መሪዎች፣ ከሲቪል ማሕበረሰቡ አባላት፣ እንዲሁም ጋዜጠኞች ጋር ባገር ክህደትና ሕገ መንግሥቱን ለመናድ በመሞከር ወንጀሎች ተከሰው ነበር። ማርች 23 ቀን የውጭ መንግሥታትን ጫና ተከትሎ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጋዜጠኞችና በሌሎች 13 ሰዎች ላይ የነበረውን የክህደትና የዘር ማጥፋት ወንጀሎች አንስቷል።

በዲሴንበር 2005 እና በሜይ መካከል ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ከተላለፉ የዜና ዘገባዎች በመነጨ የስም ማጥፋት፣ ሃሰተኛ መረጃ የማስተላለፍ፣ የምክትል አዘጋጁን ስም ያለመባፍ፣ የመንግሥትን ስም የማጥፋት እንዲሁም የማሳሳት ወንጀሎች የተፈረደባቸው ብዙ ጋዜጠኞች ነበሩ። የእስር ፍርዳቸውም ከ3 ወር እስከ 18 ወራት ድረስ ይደርስ ነበር። ጥቂቶቹ የተፈረደባቸው ጋዜጠኞች ከጥቂት ሳምንታት ወይም ወራት የእስር ቆይታ በኋላ በዋስ ተለቀዋል። የዋስትናዎቹም መጠን ከ487 ብር እስከ 10,962 ብር ይደርስ ነበር። ቀደም ሲል ባመቱ በዋስ የተለቀቁት ጋዜጠኞች በጥቅምትና በኖቬምበር ፍርድ ቤት ቀርበው ነበር።

ኖቬምበር 10 ቀን ስርጭቱ የተቋረጠው በየሣምንቱ ይታተም የነበረው የአማርኛ ቋንቋ ጋዜጣ "የአገሬ" ዋና አዘጋጅ አቶ ጌታቸው ስሜ በዲሴንበር 2005 የተፈረደበትን የሥም ማጥፋት ፍርድና የ3 ወር የእስር ቅጣት ይግባኝ ለማለት ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረ ቢሆንም የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ውድቅ አድርጐበታል።

የሳምንታዊው የ"ዳግም ወንጭፍ" ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና አሣታሚ የነበረው አቶ ለይኩን እንግዳ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ይግባኝ መሠረት የ1,000 ብር ዋስ ጠርቶ እንዲለቀቅ በጃንዋሪ 5 ቀን ተፈርዶለታል። በኖቬምበር ወር ይግባኙ ውድቅ ተደርጎ ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ተዛውሯል። የለይኩን ክስ መነሻው በዳግም ወንጭፍ በ1999 የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ስለሚባል አማፂ ድርጅት ከተፃፈው ፅሁፍ ሲሆን ይህ ፅሁፍ አማፂው ቡድን በመንግሥት ወታደሮች ላይ ወታደራዊ ድል አግኝቷል ይል ስለነበር ነው። "ዳግም ወንጭፍ" ህትመት የማግኘት ችግር ስለገጠመው ከገበያ ሊወጣ ተገዷል ተብሏል።

የፌብሯዋሪ 21 የሳምንታዊው የአማርኛ ቋንቋ ጋዜጣ "የጦቢያ" ዋና አዘጋጅ የነበረው አረጋ ወልደቂርቆስ በስም ማጥፋት ወንጀል ተከሶ በቁጥጥር ስር ዋለ። ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክሱ እንዲነሳለት ይግባኝ በማለቱ በ1,000 ብር ዋስ ተለቋል። በኖቬምበር ወርም ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ተነስቶለታል።

በማርች 8 "ፖለቲካ" ይባል የነበረው የአማርኛ ቋንቋ ሳምንታዊ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው አብርሃም ገብረኪዳን በ2002 ዓ.ም ቢቢሲን በመጥቀስ የኢትዮጵያ መንግሥት የኤርትራ ተቃዋሚዎችን ያሰለጥናል የሚል"የሃሠት ዜና" በማሰራጨቱ በአንድ አመት እስራት እንዲቀጣ ተፈርዶበት ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም በ1,000 ብር ዋስ ተለቋል። በህዳር ወርም ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ሁሉ ተነስቶለት በነፃ ተለቋል።

ባመቱ መጨረሻ በቆዩ ክሶች የተከሰሱ ሁለት ጋዜጠኞች ወሰንሰገድ ገብረኪዳንና ተሰፋለነ መንገሻ በእስር ላይ ቆይተዋል። ኤፕሪል 18 የታገደው የ "አዲስ ዜና" ዋና አዘጋጅ የበረው ወሰንሰገድ ገብረኪዳን በ2002 ላይ ከታተመ ፅሁፍ በመነጨ በስም ማጥፋት ወንጀል በ16 ወራት እስራት እንዲቀጣ ተፈርዶበታል። ይህ ፅሁፍ የኢህአዴግ ሕትመት የሆነው የ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ"ን አዘጋጅ ስም ያጠፋ ነበር ተብሏል። በፍርዱ ወቅት ወሰንሰገድ ቀደም ሲል ሕገ መንግሥታዊውን ስርዓት ለመገልበጥ በመሞከር ወንጀል ከተከሰሱት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች፣ የሲቪል ማህበረሰቡ አባላትና አስራ አራት ጋዜጠኞች መሃከል የፍርድ ሂደቱን በመከታተል በእስር ቤት ነበር።

በኤፕሪል 25 በብዙ የአማርኛ ቋንቋ ጋዜጦች በፍሪ ላንሰርነት እንዲሁም የግል ለሆነውና በየሳምንቱ በአማርኛ ታትሞ ለሚወጣው "ለአዲስ አድማስ"ጋዜጣ መደበኛ የአምድ ፀሃፊ የነበረው አብርሃም ረታ ባንድ አመት እስራት እንዲቀጣ ተፈርዶበት በዚያው ዕለት ወደ እስር ቤት ተወስዷል። አብርሃም የተከሰሰው "ሩህ" በተሰኘውና አሁን በሕትመት ላይ በሌለው የግል የአማርኛ ጋዜጣ ላይ በ2002 የመንግሥት ባለስልጣናት ከአለም ባንክ እርዳታ የተገኘ ገንዘብ ዘርፈዋል የሚል ፅሁፍ በመፃፉ ነበር። አብርሃም ጉዳዩን ለፌደራሉ ጠቅላይ

ፍርድ ቤት ይግባኝ ብሎ በኖቬምበር ወር ፍርድ ቤት ቀርቦ ጉዳዩ በቀጠሮ እንደተያዘ ቆይቶ ባመቱ መጨረሻም በእንጥልጥል ላይ ነበር።

ሜይ 4 የቀድሞው ሣምንታዊ አማርኛ ጋዜጣ "የመብሩክ" አዘጋጅ የነበረው ተሰሃለኝ መንገሻ በስም ማጥፋት ወንጀል ተከሶ በ16 ወራት አስራት እንዲቀጣ ተፈርዶበታል። ጉዳዩ በ "መብሩክ" ላይ በኢትዮ-ኤርትራው የ1998-2000 ጦርነት ወቅት ከተፃፈ ፅሁፍ የመነጨ ነበር። ተሰሃለኝ ቀደም ሲል በትንሹ ሶስት ጊዜ በ1997 እና በ2000 ዓ.ም መሃከል በ "መብሩክ" ላይ ከሰራቸው ስራዎች ጋር በተያያዘ ታስሯል። ተሠሃለኝ ከዚህም በተጨማሪ ሌላ በንጥልጥል ላይ ያለ የቀድሞው "መብረቅ" ጋዜጣ ላይ በ1995 የግብፁ ሆስኒ ሙባረክ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ስብሰባ ለመካፈል በመጡ ጊዜ የተደረገባቸውን የግድያ ሙከራ በተመለከተ "የተሳሳተ መረጃ" በማቅረቡ ክስ ይጠብቀው ነበር።

በፌብሯዋሪ 19 ሣምንታዊውና በአማርኛ ይታተም የነበረው የተቃዋሚ የግል ጋዜጣ የ "ልሣነ ሕዝብ" ስራ አስኪያጅ የነበረው ጐሹ ሞገስ ፖሊስ "ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር የተያያዙ አሸባሪዎችን የመመንጠር ስራ" ባለው ሁኔታ ተይዞ ታስሯል። ጐሹ ሞገስ ሕገ-መንግሥቱን "ለመናድ፣ ለመለወጥ፣ ወይም ለመሻር" በመፈለግ ተከሷል። ባመቱ መጨረሻም የዋስ መብቱን ተነፍጐ በእስር እንዲቆይ ተደርጓል። "ልሳነ ሕዝብ" በግልፅ በመንግሥት የታገደ ባይሆንም ከኖቬምበር 2005 ጀምሮ ግን ለመታተም ሳይችል ቆይቷል። ይሄም የሆነው የጋዜጣው አመራሮች በመታሰራቸውና የቀሩትም ሠራተኞች እስራትን በመፍራታቸው ነው።

የ"ሳተናው" ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረውና ከቅንጅት መሪዎች ጋር የፍርድ ሂደታቸውን ከሚከታተሉት 16 ጋዜጠኞች አንዱ የሆነው እስክንድር ነጋ በተለየ እስር ቤት ውስጥ ባንድ ክፍል ለብቻው ተዘግቶበት ታስሮ ነበር። የእስክንድር ጓደኛ የሆነችው ጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ታስራ ትገኛለች። ከ16ቱ ጋዜጠኞች አንዱ የሆነውና የሳምንታዊው የ "ኢትኦጵ" ጋዜጣ አሳታሚ የነበረው ሲሳይ አጌና በኦገስት ወር ወደ ከርቸሌ ተዛውሮ በጨለማ ክፍል ተዘግቶበት ነበር። (ክፍል 1 መን ይመልከቱ)

ጃንዋሪ 2005 የመንግሥት ሰዎች ሺፈራው ኢንሰርመ የተባለውን በመንግሥት ቁጥጥር ስር ባለው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የኦሮምኛ ቋንቋ ዝግጅት ክፍል የሚሠራውን ጋዜጠኛ ለሶስተኛ ጊዜ በቁጥጥር ስር በማዋል አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የወንጀል ምርመራ ቢሮ እስር ቤት አስረውታል። ሺፈራውና በኤፕሪል 2004 የታሠረው ሌላው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ የሆነው ደበሳ ዋቅጅራ በተለያዩ ክሶች ምክንያት በእስር ቆይተዋል። የተከሰሱባቸው ወንጀሎች የመንግስትን መረጃ ለኦነግ የማስተላለፍ ወንጀልን ይጨምራሉ። የማረሚያ ባስልጣናት እስረኞቹ እንዲፈቱ የሚያዙ ብዙ የፍርድ ቤት ትዕዛዞችን አላከበሩም ነበር።

ፖሊስ "የአዲስ ዜና" ዋና አዘጋጅ የበረውን ፋሲል የኔአለምን በሜይ 2005 የቅንጅት አመራሮችን ለማሰርና ለመግደል ገዝተው ፓርቲ ኢሕአዴግ ልዩ የመረጃ ሃይል አቋቁሟል። እንዲሁም 11 የትግራይ ሴቶችን የቅንጅት አመራሮችን በመርዝ እንዲገድሉ መልምሏል በሚል ለፃፋቸው ፅሁፎች መረጃ ያቀበሉትን ምንጮች እንዲጠቁም ጠይቆት የነበረ ሲሆን ፋሲል ግን ማንነታቸውን ባለመግለፁ ማረጋገጫ የሌላቸው ዜናዎችን በማሳተም ክስ ተመስርቶበት ታስሯል።በኋላም በ2005 በዋስ የተለቀቀ ቢሆንም በኋላ ከቅንጅት አመራሮች ጋር ፀረ መንግሥት ወንጀሎችን ፈጽማችኋል ተብለው ከታሠሩት 16 ጋዜጠኞች አንዱ ነበር። እስከ አመቱ መጨረሻም በእስር ቤት ቆይቷል።

በጁን 2005 በአዲስ አበባ ጋዜጣዎችን የሚያከፋፍለውን ፍቅሬ ጉዱን የመንግሥት የፀጥታ ሃይሎች ለአንድ ወር አስረው አቆይተውታል። ከተፈታ በኋላ "አስኳል" ለተባው በየሳምንቱ ለሚታተመው የግል የአማርኛ ጋዜጣ ቃለ መጠይቅ ሰጥቶ ነበር። በቃለ መጠይቁም ወቅት ስለ እስሩ አብራርቶ ገልፆ ነበር። ከከተማ ውጪ ታስሮ

በነበረበት ወቅት የእስር ቤቱ ይዞታ በጣም መጥፎ እንደነበረና መንግሥትም ስላሰረው ወቀሳውን አቅርቦ ነበር። በኦገስት 2005 እንደገና ታሰረ። ካራት ቀናት የፖሊስ እስር በኋላ በዋስ ተለቀቀ። ለመታሰር ያበቃው ፖሊስ ቃመጠይቁን የሃሰት መረጃ ለማስተላለፊያና የፖሊስንና የማረሚያውን አሠራር ለማንቋሸሽ ተጠቅሞበታል በሚል ስለከሰሰው ነበር። የፍቅሬ ጉዳይ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ምንም መረጃ የለም።

ሁሉም የመንግሥት የመገናኛ ብዙሀን የመንግሥት ድጐማ ተደርጐላቸዋል። ይሁን እንጂ የመንግሥት መገናኛ ብዙሀን ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደርና በከፊል ገቢ ለማስገባት ህጋዊ ድጋፍ አላቸው። የማስታወቂያ ሚኒስቴር የመነግሥት ቃል አቀባይ ነበር። ስለሆነም በመንግሥት፤ በፕሬስና በህዝቡ መሃከል ያሉ ግንኙነቶችን ያሳካል። ሆኖም ግን መንግሥት ከግሉ ፕሬስ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እምቢተኛ ከመሆኑም በላይ ትብብሩ በመንግሥት◉ ከሚመራው ከኢዜአና በኢሕአዴግ ቁጥጥር ስር ካለው ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል እንዲሁም ከውጪ የዜና ድርጅቶች ዘጋቢዎች ጋር ብቻ የተወሰነ እንዲሆን አድርጐ ነበር።

ካለፉት አመታት በተለየ የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ ለተወሰኑ ነፃ ጋዜጦች በተወሰነ መልኩ በአፊሴላዊ ዝግጅቶች ላይ እንዲገኙ ፈቅዷል። ሚያዝያ 30 በ14 ዓመታት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የነፃው ጋዜጦች ጋዜጠኞች ከመንግሥትና አለም አቀፍ ጋዜጠኞች ጋር በጠቅላይ ምኒስትሩ የተሰጠውን መግለጫ እንዲዘግቡ ተጋብዘዋል። ባመቱ መጨረሻ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚታተሙ ነፃ ጋዜጦች ጋዜጠኞች በሶማሊያ ላይ በታህሣስ ወር ጠቅላይ ምኒስትሩ ለውጪ ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ላይም እንዲገኙ ተጋብዘው ነበር።

ማንኛውም ጋዜጣ ለህትመት ፈቃድ ሲመዘገብ የ10,000 ብር የባንክ ሂሳብ ማረጋገጫ ሊኖረው እንደሚገባ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ያስገድዳል። ይህ የገንዘብ መጠን ትናንሽ አታሚዎችን እንዳይመዘገቡ ያገደ ነበር። አሣታሚዎችም አንድ ጋዜጣ ለማቋቋምና ለማካሄድ ቋሚ ነዋሪዎች መሆን ይገደዱ ነበር። መንግሥት ለሌሎች የንግድ ባለቤቶች ቋሚ ነዋሪነትን እንደግዴታ አያስቀምጥም። ስለሆነም አንዳንድ ነፃ ጋዜጠኞች መንግሥት ይህንኑ ግዴታ ለማስፈራሪያት እንደተጠቀመበት ይናገራሉ። የፕሬስ ህጉ ሁሉም አሣታሚዎች ጋዜጦቻቸው በታተመበት ቀን የጋዜጦቻቸውን ቅጂ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ማቅረብ እንዳለባቸው ይገልፃል።

አብዛኞቹ የግል ጋዜጦችም ሆኑ የመንግሥት ጋዜጦች በመንግስት ማተሚያ ቤቶች ነበር ጋዜጦቻቸውን የሚያሳትሙት። የህዳር 2005 ቱን አለመረጋጋት ተከትሎ ማተሚያ ቤቶች የተወሰኑ ጋዜጦችን የፍትሕ ሚኒስቴር ማተሚያ ቤቶች ላተሟቸው ጋዜጦች ይዘት ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ መግለጫ በማውጣቱ ምክንያት አናትምም ይሉ ነበር። ፖሊስ ማንኛውንም ማተሚያ ቤት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የመዝጋት ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር። ነገር ግን ይህን ሥልጣኑን ባመቱ ውስጥ ስራ ላይ አላዋለውም ነበር።

የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞች ማህበር (ኢነጋማ) መንግሥት በግሉ ፕሬስ ላይ በወሰደው ርምጃ የተነሳ እንደተበታተነ ነበር። ብዙ ጋዜጠኞች፤ የኢነጋማውን ፕሬዚዳንት ክፍሌ ሙላትን ጨምሮ፤ በስደት ላይ ነበሩ። መንግሥት ክህደትና የዘር ማጥፋት ሙከራ ባለው ወንጀል ከሚፈለጉት ስዎች ስም ውስጥ የሱም ስም ይገኝበት ነበር። የብዙዎቹ አባላቱ መታሠር ኢነጋማ እንዳይንቀሣቀስ ገድቦት ነበር። ሌላው በመንግሥት ድጋፍ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ብሄራዊ ህብረት የተባለው ማህበርም ባመቱ ምንም እንቅስቃሴ አላደረገም ነበር።

የመረጃ መረብ (የኢንተርኔት) ነፃነት

ከግንቦት አጋማሽ ጀምሮ ብዙ በመረጃ መረብ ይለቀቁ የነበሩ ዕሁፎችና የሚዲያ ነፃነት ተሟጋቾች እንደሚሉት መንግሥት ልዩ ልዩ መንግሥትን የሚተቹ ድረ-ገፆችን መከልከል ጀምሮ ነበር። ይህ ክስ በአዲስ አበባ ነዋሪዎችም የተረጋገጠ ነበር። ከታገዱት ድረ-ገጾች መካከል የኦነግ ድረ-ገፅን አካትቶ በውጭ በሚኖሩ

ኢትዮጵያዊያን የሚመሩ ብዙ የዜና ፅሁፎችና ድረ-ገጾች ተዘግተዋል። ከነዚህም መካከል ኢትዮጵያን ሪቪው፣ ሳይበር ኢትዮጵያ ዶትኮም፣ ቋጠሮ የአማርኛ መጽሄት፣ ትንሳኤ ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ሚዲያ ፎረም ይገኙበታል። ለጋዜጠኞች ከለላ በመስጠት የሚታወቀው ዚ ኮሚቲ ቱ ኘሮጀክት ጀርናሊስትስ /ሲፒጄ/ የተሰኘ ውን ድርጅት እና ሌሎች መነግሥት እነኚህን ድረ-ገጾች ማገድ እንዲያቆም ጠይቀው ነበር። የማስታወቂያ ሚኒስቴር ባለስልጣናትም ስለተከሰተው ድንገተኛ የድረ-ገጽ ዕግድ ምንም እንደማያውቁ፣ መረጃም እንደሌላቸውና የመንግሥት እጅ እንደሌለበት ገልፀዋል።

በታህሳስ 2005 በድረ-ገጽ የሚሠራጨው የኢትዮጵያን ሪቪው አሣታሚ የነበረው ኤሊያስ ክፍሌ በሌለበት የክህደት ክስ ቀርቦበታል። ለዚሁ ድረ-ገጽ ከአዲስ አበባ ሪፖርት ታደርግ የነበረችው ፍሬዘር ነጋሽ ያለክስ ከጥር 27 እስከ መጋቢት 8 ታስራ ነበር።

ሲፒጄ መንግሥት በተለመደው የህትመት መገናኛ ላይ የወሰደው ርምጃና እሱንም ተከትሎ ያጋጠመው ሰፊ የራስ በራስ ሳንሱር ብዙ ጋዜጠኞችንና የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን በኢንተርኔት እንዲጠቀሙ አስገድዷቸዋል ይላል።

ታህሳሥ 24 "ካፒታል" የተባለው በእንግሊዘኛ ቋንቋ በየሣምንቱ የሚወጣ የግል ጋዜጣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽንስ ኤጀንሲ ለኢንተርኔት ካፌዎች የኢንተርኔት ተጠቃሚዎቻቸውን የሚመዘግቡበት ቅጽ እያደለ እንደነበረ ዘግቧል። የዜና ምንጮቹ ለ "ካፒታል" እንደገለፁት የቴሌኮሙኒኬሽንስ ኤጀንሲ ከፌደራል ፖሊስ ጋር በመሆን ህገ-ወጥ ተጠቃሚዎችን ለመለየት በአዲስ አበባና በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ ፎርሙን ለሁሉም የኢንተርኔት ካፌዎች ሲያሰራጭ ነበር። እነዚሁ ምንጮች እንደገለፁት ማንኛውም ኢንተርኔት ካፌ ያልተመዘገቡ ሠዎችን ሲያስተናግድ ቢገኝ ባለቤቱ ይታሠራል።

እንደሚዲያ ዘገባዎች ዜጐች ኢንተርኔትን በቋሚነትና በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ። ከዚህም በላይ የኢንተርኔት ካፌዎች መበራከት ደግሞ የኢንተርኔት አቅርቦቱን በከፍተኛ ደረጃ አሣድጐታል። የኢንተርኔት ስልክም ውጪ ካሉ ቤተሰቦቻቸው ጋር መገናኛ መንገድ ስለነበር ከፍተኛ ተቀባይነት ነበረው። እንደ "ካፒታል" ሪፖርት በ2004 መጨረሻ በአዲስ አበባ ብቻ የኢንተርኔት ተጠቃሚው ቁጥር በግምት ወደ 100,000 አካባቢ ይጠጋ ነበር። በግምት 94 በመቶ የሆኑት የዛገሪቱ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች በአዲስ አበባ የሚገኙ ነበሩ፣ ይህ ደግሞ ከዋና ከተማዋ ውጪ ያለውን የቴሌኮሙኒኬሽንስ መሠረተ ልማት ውስንነት ጠቋሚ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ "ካፒታል" የቴሌኮሙኒኬሽንስ ኮርፖሬሽን የኢንተርኔት አገልግሎቱን ቀላልና በተመጣጣኝ ክፍያ በማቅረቡ ግለሰቦች የዳይል አኘ ኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረጉን ሪፖርት አድርጓል። ባመቱ መጨረሻም ባገሪቱ 40,000 ሰዎች በየቤቶቻቸው የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ሆነዋል።

የሞባይል ስልክ የፅሁፍ መልዕክት አገልግሎት በብቸኛው የመንግሥት ቴሌኮሙኒኬሽንስ እንደታገደ ቀጥሏል። ተቃዋሚው ቅንጅት ፀረ-መንግሥ ተግባራትን ለማስተባበር ተጠቅሞበታል በሚል ነበር ዕግዱ የተደረገው።

የአካዳሚክ ነፃነትና ባህላዊ ዝግጅቶች

ባለፈው ዓመት መምህራን የፖለቲካ አቋም ሊኖራቸው አይገባም በሚል መንግስት የአካዳሚክ ነፃነትን ገድቦ ነበር። ባለስልጣናት በየትኛውም ደረጃ ያሉ መምህራን ከትምህርት ዕቅዳቸው ውጪ ምንም ዓይነት ሥራ ሊሰሩ እንዳይችሉ ከመከልከላቸውም በላይ በዩኒቨርሲቲ ግቢዎች ውስጥ ማንኛውም አይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴና አደረጃጀት እንዳይደረግ ጫና ያደርጉ ነበር። ባመቱ ሙሉ የደንብ ልብስ የለበሱና በሲቪል ልብስ የሚንቀሳቀሱ ፖሊሶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ግቢ ውስጥና ውጪ እንደነበሩ ተዘግቧል። ባለፈው ዓመት መንግሥት መምህራንና ተማሪዎችን በቁጥጥር ስር አውሏል። መምህራንና

ተማሪዎች ከመንግሥት አቋምና እምነት የተለየ አቋም እንዲኖራቸው አይበረታቱም ነበር። በአካዳሚያዊ ውሳኔዎች ላይ ግልፅነት ባለመኖሩ በአካዳሚክ ህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ውሳኔዎች በዘር ወይም በሃይማኖት የተቃኙ ነበሩ ብለው ያማርሩ ነበር። የመናገር፣ ራስን የመግለፅና የመሰብሰብ መብቶች በዩኒቨርሲቲና ሁለተኛ ደረጀ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተደጋጋሚ ተገድበዋል።

መስከረም ላይ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ትያትር ሊቀርብ የነበረ "ወይ አዲስ አበባ" የተሰኘ ሙዚቃዊ ድራማ በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንዳይታይ ታግዷል። የድራማው ፅሁፍ የተፃፈው በፀሃፊ ተውኔት ጌትነት እንየው ነበር። የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ባለስልጣናት ድራማው ለህዝብ ክፍት ከመደረጉ በፊት በተደረገ ቴክኒካል ልምምድ ላይ ተገኝተው ነበር።

ለ. *ሠላማዊ ስብሰባ የማድረግና በማህበር የመደራጀት መብት*

ሕገመንግስቱም ሆነ ሕጉ የመሰብሰብን መብት ያረጋግጣሉ። ከግንቦት 2005ቱ አገራዊ ምርጫ በፊት በዛ ያሉ የተቃውሞ ሰልፎች ተካሂደው ነበር። በአዲስ አበባም ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ቁጥር ያለው ሕዝብ የተሳተፈበትና ከምርጫው በፊት በዋለው እሁድ የተደረገው ሰልፍ አንዱ ምሣሌ ነበር። ይሁን እንጂ ከምርጫው ማግስት ጀምሮ አመቱን ሙሉ መንግሥት ይህንን መብት በተግባር ገድቦት ነበር። ከግንቦት 2005 እስከ አመቱ መጨረሻ መንግሥት አንድ ህዝባዊ ሰልፍ ብቻ እንዲደረግ ፈቅዶ ነበር።

ትልቅ ህዝባዊ ስብሰባዎችንም ሆነ ሰልፎችን የሚያዘጋጁ አካላት ከስብሰባው ወይም ከሰልፉ 72 ሰዓታት በፊት ለመንግሥት አሣውቀው ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሪፖርት እንዳደረጉት ባመቱ ውስጥ ደጋፊዎቻቸው ስብሰባዎችን ተካፍለው በሚወጡ ጊዜ በተደጋጋሚ ለፖሊስ ወከባና ጥቃት ተጋልጠው ነበር። በኢሰመጉ ሪፖርት መሠረት የአዲስ አበባን ክልላዊ መስተዳድር ጨምሮ የክልል መንግሥታት ሠላማዊ ስብሰባ የማድረግና የመደራጀት መብትን ሲገድቡ ነበር።

ኦፌዴንም የኢህአዴግ ካድሬዎች የኦፌዴን አባላትን የአባልነት መታወቂያ ካርድ በመቀማት ማጥፋታቸውን፣ የኦፌዴንን ስብሰባዎች መረበሻቸውንና የኦፌዴን አባላትን በፖሊስ ጣቢያዎችና በጦር ሠራዊት ካምፖች ማሠራቸውን ሪፖርት አድርጓል።

በ2004 ላይ የኦሮሚያን ዋና ከተማ ከአዲስ አበባ ወደ አዳማ እንዲዛወር ያደረገውን የመንግሥት ውሣኔ በመቃወም ሰልፍ ያደረጉትን ሰልፈኞች ደብድበዋል በተባሉትም ሆነ በዚያው አመት ላይ በመቶ የሚቆጠሩ ተቃውሞ ያሰሙ ተማሪዎችን በኮረት ላይ እንንዲንበረከኩና ባዶ እግራቸውን እንዲሮጡ ባስገደዱት ፖሊሶች ላይ የተወሰደ ምንም እርምጃ አልነበረም። (ክፍል 1ሐን ይመልከቱ) ባመቱ መጨረሻም ባለፉት አመታት ህጋዊ ያልሆኑ ስብሰባዎችን በማድረግ የተያዙ ስዎች በእስር ይቆዩ አይቆዩ የታወቀ ነገር አልነበረም።

ባመቱ ውስጥ ባብዛኛው ምንም የመሰብሰብ ፍቃዶች ባለመሠጠታቸውና ህገ-ወጥ ሰልፎችም ውሱን ስለነበሩ በፖሊስ፣ በጦር ሰራዊቱና በሚሊሺያዎች በተቃዋሚ አባላትና በህዝቡ ላይ ይደርሱ የነበሩ ጥቃቶች ቀንሰው ነበር።

የመደራጀት መብት

ሕጉ የመደራጀትን መብትና በማንኛውም ሰላማዊ የፖለቲካ ተግባር የመሣተፍን መብት ያረጋገጠ ቢሆንም በተግባር ግን መንግሥት እነዚህን መብቶች ገድቦ ነበር። የፍትህ ሚኒስቴር መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን

የሚመዘግብና ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን በነዚህ ድርጅቶች የምዝገባ ሂደት ግልፅነት አኳያ የተወሰነ መሻሻል ታይቶ ነበር። ይሁን እንጅ መንግሥት ለሰብአዊ መብት ሲባ ፍቃድ መከልከሉን ቀጥሎ ነበር። (ክፍል 4ን ይመልከቱ)

በሕጉ በተፈቀደው መሠረት መንግሥት የፖለቲካ ፓርቲዎች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲመዘገቡ ያስገድዳል። በ2005 የምርጫ ቦርዱ በተከታታይ የተቀዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ እንቅስቃሴዎች በሚገድቡ ውሳኔዎች፣ የቅንጅትን መዋሃድ መከልከሉንና ከምርጫውም በኋላ ቅንጅቱን ለመቀበል ባለመፈለጉ ገለልተኛነቱ ጥያቄ ውስጥ ወድቆ ነበር። ይሁን እንጂ ባመቱ ውስጥ የምርጫ ቦርድ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲን መዝግቧል። ይህ ፓርቲ® ፓርላማን በተቀላቀሉት የቅንጅት አባላት የተቋቋመ ነው። የምርጫ ቦርድ በኦብኮ የተደረገውን የአመራር ለውጥ ባለመቀበሉ የፓርቲውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንደገደበ ቀጥሏል።

ባመቱ ውስጥ ህብረት፣ ቅንጅትና ኦብኮ በመላው የሃገሪቱ ክፍሎች አባሎቻቸው እንደታሠሩና ብዙ የፖለቲካ ፓርቲ ቢሮዎች መዘጋታቸውን ሪፖርት አድርገዋል። (ክፍል 1 መን ይመልከቱ) መንግሥት የዋናዎቹን ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አመራር አካላት በማዋከብ እንዲሁም የመንግሥት ቢሮዎች እነዚህ የአመራር አካላት በፓርቲዎቻቸው ላይ ያላቸውን ስልጣንና አባልነት ለመገደብ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ይጠቀሙ እንደነበር የሚገልፁ ታማኝ ሪፖርቶች ነበሩ።

ባመቱ ውስጥ የፌደራል የክልል ፓርላማ አባላትን ጨምሮ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ወደ መረጣቸው ህዝብ እንዳይሄዱና ደጋፊዎቻቸውን እንዳያገኙ ተከልክለው ነበር። የፌደራሉ ፓርላማ አባል የነበሩት የኦፌዴን ፕሬዚዳንት በኦሮሚያ ክልል የሚገኘውን የትውልድ ቦታቸውን የቦጂ ዲርመጂን ከተማ እንዳይጎበኙ ከመታገዳቸውም በላይ ለመሄድ ሲሞክሩ ባካባቢው ፖሊሶች ዛቻና ማስፈራራት ደርሶባቸዋል። በተጨማሪም ከ42 የኦብኮ የፌደራል ፓርላማ አባላት ውስጥ 3ቱ ብቻ ነበሩ ባመቱ ውስጥ ከመረጣቸው ህዝብ ጋር መገናኘት የቻሉት። እነኚሁ 3ቱ የኦብኮ የፓርላማ አባላት ሪፖርት እንዳደረጉት ከሆነ ካካባቢው ተወካዮች ጋር ስብሰባ ካደረጉ በኋላ የፓርቲው አባላት ባካባቢው የፀጥታ ሃይሎች ተዋክበዋል፤ ታስረዋል።

በ2004ቱ የሜጫና ቱለማ ማህበር አገዳ እንዲሁም በአባሎቹ እስር ጉዳይ ላይ ምንም የተሰወጠ ነገር የለም። የተወሰኑት እስሮች ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተደረጉ ነበሩ ።ሆኖም የተወሰኑት ተጠርጣሪዎች ምንም እንኳን ፍርድቤት እንዲለቀቁ ቢያዝም በእስር ቆይተዋል። (ክፍል 1 መን ይመልከቱ)

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ስብሰባ ለማድረግ በሞከረ ጊዜ ሁሉ የመንግሥት አገዳዎች ያጋጥሙት ነበር። ነሐሴ 30 ቀን ፖሊስ የኢመማ መሪዎችን ሃገራዊ ስብሰባ አቋርጦ ዶኩሜንቶችንና ሌሎች ዕቃዎችን ወስዶ ነበር። ያካባቢው ፖሊሶች ስብሰባው የተደረገበትን አዳራሽ ከተቆጣጠሩት በኋላ አሸገውት ነበር። ይሁን እንጂ ፖሊስ አብዛኛውን የወሰዳቸውን ዕቃዎች መልሷል።

ይህ ሁኔታ መንግሥት በተከታታይ የኢመማን እንቅስቃሴ ውሱን ለማድረግ ከሞከረ በኋላ የሆነ ነበር። ኢመማ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ የነበረ ቢሆንም በ1993 ኢህአዴግ ሥልጣን በያዘ ወቅት ኢህአዴግን የሚደግፍ ተለዋጭ ኢመማ ተቋቁሞ ነበር። በ1993 ነባሩ ኢመማና በመንግሥት የሚደገፈው ኢመማ በስምና ንብረት መብት ላይ ረጅም ጊዜ የወሰደ የክስ ሂደት ጀምረው ነበር። ምንም እንኳ ነባሩ ኢመማ በዝቅተኛ ፍርድ ቤቶች የተፈረደለት ቢሆንም አዲሱ ኢመማ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ጠይቋል። በዚህም ወቅት የፀጥታ ሃይሎች የነባሩን ኢመማ ቢሮዎች በመዝጋት አባሎቹን ማዋከብ ቀጥለው ነበር።

ሐ. የሃይማኖት ነፃነት

ሕገመንግሥቱና ሕጉ የሃይማኖት ነፃነትን ያረጋግጣሉ። መንግሥትም ባጠቃላይ ይህን መብት በተግባር አክብሮ ነበር። ይሁን እንጂ የክልል ባለስልጣናት አልፎ አልፎ ሲጥሱት ታይቷል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና እስልምና ዋናዎቹ ሃይማኖቶች ናቸው።

ወደ 90 በመቶ የሚቆጠረው ህዝብ የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታይ ነው። ምንም እንኳን ባለፈው ዓመት መንግሥት የሃይማኖት ተቋማት በፍትህ ሚኒስቴር እንዲመዘገቡ ቢያስገድድም አንመዘገብም ባሉት ተቋማት ላይ ግን ስለተወሰደ ርምጃ የተደረገ ሪፖርት የለም። በህጉ መሠረት ማንኛውም የልማት ሥራ የሚሠራ የሃይማኖት ተቋም የልማት ስራ የሚሠራውን ክፍል እንደ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት (መያድ) ሊያስመዘግብ ይገደዳል። መንግሥት ለውጪ የሃይማኖት ሠራተኞች ከሃይማኖት ተቋም የልማት ክፍል ጋር ካልተዛመዱ በቀር የሥራ ፈቃድ አይሰጥም ነበር።

ባመቱ መጨረሻም በመንግሥቱ መንግስት (ደርግ) ተወርሰው የነበሩ ጥቂት የሃይማኖት ተቋማት ንብረቶች አልተመለሱም ነበር።

ማህበረሰባዊ ጥቃቶችና አድልዎ

አናሳ የሃይማኖት ቡድኖች ለሃይማኖት ቦታዎች በሚፈቀድ የመንግሥት መሬት አደላደል ላይ አድልዎ እንደነበረ ሪፖርት አድርገዋል። ባለሥልጣናት የአመራር አካል አባላት ከአነግና ከሜጫና ቱለማ ማህበር ጋር ግንኙነት አላቸው ያሉውን አንድ ተፈጥሮ ሁሉ ነፍስ እንዳለው የሚያምን የኦሮሞ አማኞችን ቡድን አግዷል። የፕሮቴስታንት ቡድኖች ለቤተርስቲያን መሥሪያና ለመቃበር ቦታ መሬት በሚጠይቁ ጊዜ ያካባቢ ባለስልጣናት አድልዎ እንደሚያደርጉባቸው ሪፖርት አድርገዋል።

የኢቫንጂሊካል መሪዎች እንደገለፁት ባለስልጣናት እንደ "መጤ" ስለሚቆጥሯቸው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባዔ ጋር ሲተያይ በመሬት ድልድል ተጐጂዎች ነበሩ። የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ አንዳንዶች መንግስት ለነሱ የሚያደላ ቢመስላቸውም መሬት ለማግኘት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤትክርስቲያን በበለጠ እንደሚቸገሩ ሪፖርት አድርገዋል። ባለስልጣናት ህገወጦች ከመንግሥት ፈቃድ ውጪ የገነቧቸውን መስጊዶች ለማፍረስ ኢላማ አድርገዋቸው ነበር።

በመስከረም መጨረሻና በጥቅምት መጀመሪያ ላይ በሙስሊሞችና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች መካከል በጅማ አካባቢ ተከስተው የነበሩት ግጭቶች ለ12 ሰዎች ህይወት መጥፋት እንዲሁም ለብዙ ቤተክርስቲያናትና ቤቶች መቃጠል ምክንያት ሆነው ነበር። ብጥብጦቹ የተጀመሩት በመስቀል በዓል ዋዜማ በሴፕቴምበር 26 የበራው ደመራ ጭስ ባካባቢው ባለ አንድ መስጊድ ውስጥ በመግባቱ ነበር። ይህ ሁኔታም በዛ ባሉ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መሃከል ሃይለኛ ጠብ በመቀስቀሱ ለሰምንት ሰዎች ሞት፡ ለቤተክረስቲያናትና ቤቶች መቃጠል ምክንያት ከመሆኑም በላይ ያካባቢው ፖሊሶችም ግጭቱን ተከትሎ ሙስሊሞችን በጅምላ አስረው ነበር። ጥቅምት 4 ቀን ባንድ ቅርብ መንደር ሙስሊሞች የኢትዮጵያ ኦርቶኮክስ ቤተክርስቲያንን ሰብረው ገብተው እሳት በለቀቁበትና ምዕመናኑን በገጀራ ባጠቁበት ጊዜም 4 ተጨማሪ ሰዎች ሞተዋል። ፖሊስ ብዙ ሰዎችን በቁጥጥር ስር ያዋለ ቢሆንም ባመቱ መጨረሻ ላይ በሁለቱም ጉዳዮች የተከሰሱ ሰዎች ላይ ፍርድ ቤት ምንም እይነት ፍርድ አልሰጠም ነበር።

ሐምሌ 24 በአዲስ አበባ ወደ መስጊድነት የተለወጠውን ህንፃ ተገቢ የግንባታ ፈቃድ የለውም በማለት የከተማው አስተዳደር አፍርሶታል። በሚቀጠሉት 3 ተከታታይ ዓርቦችም ያካባቢው ሙስሊሞች በአዲስ አበባ ድርጊቱን ተቃውመው ሰልፍ በማድረጋቸው ከፀጥታ ሃይሎች ጋር በተፈጠረው ግጭት የሰልፍ አድራጊዎች መታሰርና

ቀላል የመቁሰል አደጋዎች ደርሰውባቸዋል። የከተማው አስተዳደር ለሙስሊሙ ማህበረሰብ መስጊድ መስሪያ የሚሆን መሬት በተለዋጭ ቦታ በመስጠቱ ችግሩ ሊፈታ ችሏል።

የአይሁዱ ማህበረሰብ በግምት ወደ 2000 ይደርስ ነበር። ምንም አይነት ፀረ-ሴማዊ ድርጊት ሪፖርት አልተደረገም። ለበለጠ ማብራሪያ የ2006ቱን አለምአቀፍ ሃይማኖታዊ ነፃነት ሪፖርት ይመልከቱ።

መ. ባገር ውስጥና ወደ ውጪ የመንቀሳቀስ እንዲሁም ወዳገር የመመለስ መብቶች

ምንም እንኳን ህጉ እነዚህን መብቶች ያረጋገጠ ቢሆንም በተግባር ግን መንግሥት የተወሰኑትን መብቶች ገድቦ ነበር።

አመቱን ሙሉ መንግሥት በጋምቤላ ክልል የሚኖሩትን ተጓጉች ደህንነት ለመጠበቅ ነው በሚል ምክንያተ የዕርዳታ እህልን እና የተራድኦ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ መቆጣጠሩን ቀጥሎ ነበር።

ህጉ የግዳጅ ስደትን ይከለክላል። መንግሥትም ማንንም ዜጋ አስገድዶ ለስደት አልዳረገም። በዛ ያሉ ሰዎች፣ 54 ጋዜጠኞችን ጨምሮ፣ በራሳቸው ፍቃድ በስደት ይገኛሉ። (ክፍል 2 ህን ይመልከቱ)

ባመቱ ውስጥ የአለም አቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴ 988 ኢትዮጵያዊያንን ከኤርትራና 83 ኤርትራዊያንን ደግሞ ከኢትዮጵያ ወደ ሃገራቸው መልሷል። ብዙ ኤርትራዊያና ኤርትራ ውስጥ የተወለዱ ኢትዮጵያዊያን በመንግሥት ተመዘግበው በየስድስት ወሩ የሚታደስ የመታወቂያ ካርድ በማግኘታቸው በሆስፒታሎችና በሌሎች ህዝባዊ አገልግሎቶች መጠቀም ችለዋል። ይሁን እንጂ ያካባቢ ባለስልጣናት ለድሆች ኤርትራዊያን የህክምና አገልግሎት መንፈጋቸውን የሚገልፁ ቅንጭብጫቢ ሪፖርቶች ነበሩ።

ባመቱ ውስጥ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን በዋናነት ከሱዳንና ከኤርትራ የመጡ ባጠቃላይ 1,800 ግለሰቦችን የያዙ 680 ጉዳዮችን አይቶ በሶስተኛ አገር የማቋቋም ተግባራት ፈፅሟል ።

ባገር ውስጥ የሚፈናቀሉ ሰዎች

ከ1998 እስከ 2000 ድረስ ከኤርትራ ጋር የተደረገው ጦርነት ወደ 350,000 ገደማ የሚሆኑ ሰዎችን ያገር ውስጥ መፈናቀል አስከትሏል። ከነዚህ ውስጥ በግምት 225,000 ውን የበጎ አድራጎት ድርጀቶች እንደገና አቋቁመዋቸዋል። የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ወደ 200,000 የሚጠጉ ባገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች እንዳሉ ገምቶ ነበር። እነዚህም በግምት 62,000 በትግራይ ክልል፣ 44,700 በጋምቤላ ክልል፣ በግምት 30,000 በቦረና አካባቢ ኦሮሚያ ክልል ውስጥ እና 50,000 በሶማሌ ክልልና በኦሮሚያ ክልል ድንበር ላይ ናቸው።

በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች መሃከል ባመቱ ውስጥ ያጋጠሙ የጎሣ ግጭቶች በሺዎች የሚቆጠሩ ግለሰቦችን ከማፈናቀላቸውም በላይ ሞትና ጉዳትም አስከትለው ነበር። (ክፍል 5 ን ይመልከቱ)

የስደተኞች ጥበቃ

ህጉ በ1951 በስደተኞች ሁኔታ ላይ በተደረገው የተባበሩት መንግስታት ስምምነት መሠረት እና በ1967ቱ ፕሮቶኮል መሠረት ለሰዎች ጥገኝነት መስጠትን ያዛል። መንግሥትም ለስደተኞች ጥበቃ ማድረግ የሚያስችል ስልት ቀይሷል። በተግባር መንግሥት ስደተኞች ቢመለሱ ስቃይ ይደርስብናል ብለው ወደሚፈሩበት ሃገር ከመመለስ በመጠበቅ የስደተኝነትና የጥገኝነት መብት ይሰጣቸዋል። ባጠቃላይ መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት ስደተኞች ኮሚሽን ጋርና ከሌሎች ሰብአዊ ርዳታ አድራጊዎች ጋር ስደተኞችንና ተመላሽ ዜጐችን በመደገፍ ይተባበራል።

ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ጋር በመተባበር መንግሥት ከሱዳን፣ ኤርትራና ሶማሌ መጥተው በ1951ዱ ስምምነትና በ1967ቱ ፕሮቶኮል መሠረት የስደተኛ መብት ለማግኘት ለማይችሉ ግለሰቦችም ቢሆን ጊዜያዊ ጥበቃ ማድረጉን ቀጥሎ ነበር።

ባመቱ መጨረሻም በግምት ወደ 97,300 ያህል ስደተኞች በሃገሪቱ ነበሩ ። ከ2005 መጨረሻ ጀምሮ ይህ ቁጥር ብዙም ለውጥ አላሳየም ነበር ። ከኤርትራ የሚመጡ ጥገኝነት ጠያቂዎች ቁጥር መጨመርን በግምት ወደ 5,000 ያህል ስደተኞች ወደ ደቡብ ሱዳን እንዲመለሱ መደረጋቸው ያጣጣዋል ።

ባመቱ ውስጥ መንግሥትና የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን በትግራይ ክልል ውስጥ አዲስ ካምኘ ለመክፈትና በሺመልባ ካምኘ እየጨመረ የመጣውን የኤትራዊያን ስደተኞች ቁጥር ለማሸጋሸግ ሞክረው ነበር ። የመጠጥ ውሃ ስላልነበረው አንድ ቦታ ከተተወ በኋላ ተጨማሪዎቹን ስደተኞች በዛው በሺመልባ ካምኘ ለማስገባትና ለአዲሱ ካምኘ መሥሪያ በተያዘው ቀሪ ገንዘብ ለአካባቢው ነዋሪዎች የጤና፣የትምህርትና የንፅሕና ኘሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ለማዋል መንግሥትና የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ተሰማምተው ነበር ። ይህም የሆነው ያካባቢው ነዋሪዎች በስደተኞቹ ቁጥር ደስተኞች አልነበሩምና ነበር ።

በጋምቤላ ክልል በብሄሮች መሃከል የተከሰተው ግጭት የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ስደተኞችን ለመጠበቅ ያደርግ የነበረውን ጥረት አወሳሰቦት ነበር። (ክፍል 5ን ይመልከቱ)

በምዕራብ የነበረው ችግር እንደነበረ ቢሆንም ለስደተኞቹ ይደረግ የነበረው የምግብ አቅርቦት እንደቀጠለ ነበር ። ይሁን እንጂ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በነበረው የጉዞ ክልከላ ምክንያት አንዳንዴ የምግብ አቅርቦቱን በተገቢው ሁኔታ መቆጣጠር አይችሉም ነበር ።

መንግሥት ሁሉም ስደተኞች በሌላ የሃገሪቱ ክልል ሊኖሩ ፍቃድ እስካላገኙ ድረስ ባብዛኛው በኤርትራ፣ሶማሊላንድና ሱዳን ድንበሮች አቅራቢያ ባሉ በተወሰኑላቸው የስደተኛ ካምፖች እንዲኖሩ ያዛል ። ከነዚህ ውጪ ለመኖር የሚፈቀደው በዋነኛነት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመማር፡ ሕክምና ለመከታተል ወይም በካምፑ ያሉ የፀጥታ ችግሮችን ለመከላከል ብቻ ነው ።